# የአርዮስ ፍሬዎች

**መልስ**

**"ለሌላ አደገኛ የጦርነት አዋጅ በወገናችን ላይ ታወጀ"**

ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ በጎልጉል ድረገጽ ላይ እራሳቸውን ተሃድሶ ብለው በሚጠሩ ነገር ግን እውነተኛ ማንነታቸው ለሰወሩት ወይንም በማንነታቸው ለሚያፍሩት ፣ የምንፍቅና አቀንቃኞች መልስ ይሆን ዘንድ ነው ። በመምህር ምህረተአብ ላይ ላቀረቡት ትችት ከሞላ ጎደል መልስ ይሆናቸዋል ብዬ አምናለሁ ።

ጸሃፊው ፤ አቤቱታውን ሲያሰማ እንዲህ ይላል ፤ ተወልደን ባደግንበት ኦርቶዶክስ በቱ ክርስትያን "የፍቅር ምሳሌ ሊሆኑ በሚችሉ አገልጋዮች ላይ የጦርነት አዋጅ ታወጀብን" ተወልደን ያደግንበት ከማለት ፤ ተዘርተን የበቀልንበት ቢል ማንነቱን ይበልጥ ይገልጸዋል ብዬ አምናለሁ ። የመወለድና የመዘራት ትርጉሙ ካልገባቸው ለማለት ነው ። ሲጀመር ይህች ቤተ ክርስቲያን ባጎረሰች የተነከሰች ከመሆኗ ጸሃፊው እራሱ ይክደዋል ብዬ አላምንም ። የሉተር ፍልፍሎችና ቅፍቅፎች ፤ እንዲሁም የመከስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ በመባል የሚታወቅ ዘላንና ሰካራም ወያኔ በለስ ቀንቶአቸው ኢትዮጵያን ከተቆጣተሩበት ጊዜ ጀምሮ አማራንና ኦርቶዶክስን አከርካሪውን ሰበርነው ፤ እያሉ ያወጁትንና የፎከሩበትን ተግባራዊ ለማድረግ ምኞታቸውን ከግብ ለማድረስ የሰሩት የስራ ውጤት ነው ። ምንም እንኳን ቢማርና ቢያውቅም ሆዱ ጭንቅላት የሆነበት አለማዊ ንዋይና ዝና ያሰከረውን ሚቹን አባ ዲያቢሎስን በቤተ ክህነት አናት ላይ አስቀምጠው አገር ማፍረስ ብቻ ሳይሆን እምነታችንንም ከስር መንግሎ ለመጣል እራሳቸውን ተሃድሶ ብለው በሚጠሩ አፍቅሮተ ንዋይ ያሸነፋቸውንና ሆድ አደር ወፍ ዘራሾችን በማሰባሰብና በማደራጀት ከምን ግዜውም በላይ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ እንደተነሳሱ ይስተዋላል ።

የምእራባውያን ንዋይ በገፍ በሚፈስላቸው ፤ የበግ ለምድ የለበሱ አሳዊ መሲሆች ፤ መጽሃፍ ቅዱስን በመሰረዝ ፤ በመደለዝ ፤ የሌለ በመጨመር ፤ ቀላል አማርኛ በሚል ቅጥ አንባሩ በጠፋ መጽሃፍ ቅዱስ ተብዬ በማወናበድ ፤ አዲሱን ትውልድ በየመድረኩ በሚወራጩ ፤ በሚደንሱ ፤ በሚንፈራገጡ ፤ ትያትረኞች ትርጉም የለሽ የአጋንንት ልሳን ትርኪ ምርኪ እየዘላበዱ ብዙዎችን ይዘው እንደጠፉ ቢታመንም ፤ "የፈሲታ ተቆጢታ" ሲሆኑ ግን ሊነገራቸው ይገባል ።

ሲጀምር ቀና የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ እንጂ በየመድረኩ የሚዘርርና አረፋ የሚያስደፍቅ መንፈስ የጨለማው መንፈስ ካልሆነ ሌላ ሊሆን አይችልም ። ልሳኑም ቢሆን የሻምፓራራ ድግግሞሽ እራሱ ተናጋሪው የተናገረውን የማያውቀው ፤ የማይሰማ ፤ የማይተረጎም ፤ ቢተረጎመምም በየጊዜው አንድ የተለመደ ቃል እየቀባጠሩ ዛሬ የሚተረጉመው ሌላ ፤ ነገ የሚተረጉመው ሌላ ፤ ስለሆነ ምንጩ ማን እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ የልጆች ጨዋታ ስለሆነ በግድ እኛን ካልመሰላችሁ ካልወረዳችሁ ብሎ ሙግት አብረን እንውደቅ ካልሆነ በቀር ሌላ ምንም ሊሆን ስለማይችል እዚያው በጸበላችሁ ።

በመጨመር የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶች ባሉበት ለመከራከርም ጥያቄ ያነሳል ጸሃፊው ፣ በውነት እነዚህ አዋቂ ነን ባዮች የያዙትን ወንጌል በርግጥ አንብበውት ያውቃሉ? አይመስለኝም! ከሆነ ግን እምነት ለመከራከሪያ እንዳልሆነ ተጽፏል የተጻፈን እንኳን አንብቦ መረዳት የተሳናቸው ፤ የዞረባቸው እንደሆነ ከጽሁፉ በቀላሉ መረዳት ይቻላል ። ብታምን ታምናለህ ፣ ባታምን ወደመሰለህ ትሄዳለህ እንጂ ካንተ ጋር ተቀምጦ የሚከራከር የሚሟገት አይኖርም ። እምነት መከራከሪያ አለመሆኑን ስታውቁ ፤ ያኔ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትክክለኛ እምነት እንደሆነች ትማራላችሁ ብዬ አምናለሁ ።

ጸሃፊውም ሆነ መሰሎቹ አንድ ሊያውቁት የሚገባ ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ መላው ዓለም በተለይም የመናፍቃኑ መሪዎችና አቀንቃኝ የሆኑት ምዕራባውያኑ ድንጋይ እየቀረጹና እንጨት እየፈለጡ በሺ የሚቆጠሩ ጣኦታትን በሚያመልኩበት ዘመን ኢትዮጵያ አንድ አምላክ ብላ በስነ ልቦና ፈጣሪን የተቀበለች ፤ ከዚያም በኦሪት ዘመን ብሉይ ኪዳንን የተቀበለች ፤ ከጌታችን ከመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ በኋላም አዲስ ኪዳንን በመቀበል በትክክለኛው እምነትና መንገድ ጸንታ የኖረች ወደፊትም እስከ ምፅዓት በዚሁ በጸናው እምነቷ ጸንታ እንደምትኖር እነ ፍራሽ አዳሽ ሳይሆኑ ዓለም የሚመሰክርላት እና ሊያውቀው የሚገባ የማይታበል ሃቅ ነው ። የመናፍቁ አባትና መሪ እንኳን ከክህደቱ በፊት ለ 1,500 ዓመታት ኦርቶዶክስ ስታስተምረው እንደቆየችና በማናቸውም ነገር እንደምትቀድመው ፤ እንደምትበልጠው እንዴት ሊሰወርባቸው እንደቻለ ግልጽ አይደለም ። ዛሬ ዛሬ "ከኋላ የመጣ አይን አወጣ" ወይንም "ምጥ ለናቷ አስተማረች" ሆነና ውሃው ሽቅብ ካልፈሰስኩ ብሎ ይሞግታል ።

ሌላው የቤት ክህነትን ልብሰ ተክህኖን መዝረፍን በተመለከተ ይሆናል ። ይህም ምንም ከእውነት የራቀ አይደለም ፤ እርግጥ የቤተ ክህነትን ልብሰ ተክህኖና የቀሳውስቱን አለባበስ ይሄው አራሱን ተሃድሶ ብሎ የሚጠራው የጴንጤው አቀንቃኝ አለአግባብ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል ። ከመደበኛው ጴንጤ ምንም የሚለያቸው ነገር ሳይኖር ለምን እራሳቸውንም ኦርቶዶክስ ብለው እንደሚጠሩ ከማንም የተሰወረ ባይሆንም ዋና አላማው ምዕመኑን ለማሳሳትና ለማወናበድ ቀላል ዘዴ ሆኖ ስለተገኘ ነው ። ስብከታቸውም ሆነ እምነታቸው እንዳለ የጴንጤው እንደሆነና ውሎና አዳራቸውም ከነሱ ፓስተሮችና ተከታዮቻቸው ጋር እንደሆነ ያደባባይ ሚስጥር ነው ። አለባበሳቸውንም እንደ መሰል ፓስተር ጓዶቻቸው ሱፍና ከረባት እንዳይለብሱ የኦርቶዶክን ቆብና ቀሚስ ያስፈለገበት አብዩ ምክንያት ለሳቱ ተኩላ በግ መስሎ መምጣቱ የግድ ስለሆነ ነው ። አላማውን ለመገንዘብ እምብዛም ምርምር አያሻም ። በማናቸውም መንገድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን አስመስሎ መቅረቡ ተቀባይነትን ሊያስገኝላቸው ስለሚችል የተኩላው መመሳሰል ግድ ይላል ። እሱ ብቻም ሳይሆን ተኩላው አስመስሎ ሊመጣና ብዙዎችን እንደሚያስት የተነገረውም ትንቢት ይፈጸው ዘንድ የግድ ነውና ።

ተኩላው በሚገርም ሁኔታ የጌታችን የመድሃኒታችን እናት የሆነችውን የድንግል ማርያምን ምስል ከሚሰበሰቡበት መጋዘን ከሰባኪያቸው ጀርባ ለምዕመናን በግላጭ እንዲታይ አድርጎ ማስቀመጥ አንዱ የማሳቻ ዘዴያቸው ሲሆን ፤ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ነገር ቢኖር ግን ስዕሏን ያስቀምጡ እንጂ ስለእመቤታችን ድንግል ማርያም በድንግልና መውለድና ፤ በድንግልና ለዘለዓለም የጸናች መሆኗን ፤ አማላጃችን መሆኗን ፤ የማይተነፍሱ ነገር ግን ስዕሏን አላግባብ

በማስቀመጥ ፤ የዋሃንን ለማሳት ፤ አይነተኛ ዘዴ አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያል ። ከዚህ ቀደም እንደምናውቃቸው መናፍቃን በግልጭ ድንግልን ፤ መላይክትንና ጻድቃንን ከመስደብ ተቆጥበው ዋና ጨዋታ አድርገው የያዙት ፤ ጭራሽ ስማቸውን ባለማንሳት ምስላቸውን ብቻ እያሳዩ ኦርቶዶክሳዊ መስሎ በመቅረብ ፤ ገድላቸውን በማዳፈን ፤ አማላጅነታቸውን ባለመመስከር ፤ የማስረሳትና የማዘናጋት ጨዋታ እየተጫወቱ እንደሆነ ለብዙሃኑ አስተዋይ እና ብሩህ አይምሮ ላለው ኢትዮጵያዊ የማይሰራ ተራ የመንደር ትያትር እየተገበሩ እንደሆነ ነጋሪ ቢያገኙና ቢነገራቸው አካሄዳቸውን ለማስተካከል ይረዳቸው ይሆናል ።

በጣም አሳዛኙ ተግባራቸው ግን እየገረፉ ለምን እንደሚያለቃቅሱ ሊገባኝ አልቻለም ። እንደሚታወቀው ተሃድሶ ተባለ ጴንጤ ያንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች እንደሆኑ ጸሃፊው እራሱ እንደማይክደው አምናለሁ ። ታዲያ ለምን ኦርቶዶክስ ተዋህዶን መስሎ መቅረብ አስፈለገ? ሁለተኛ መቼም አንድ ሰው ወይንም ቡድን በማይመስለው እምነት አዳራሽ ገብቶ የራሱን የእምነት አመለካከት እንዲሰብክ በማናቸውም የእምነት ተቋም እንደማይፈቀድ የማያውቅ ይኖራል ብዬ አልገምትም ። ታዲያ የኛ ፍራሽ አዳሾች ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤት ምን ይሰራሉ? ድርሽ እንዳይሉ ተከልክለውም ከሆነ አግባብ ነው እላለሁ ። በሶስተኛ ደረጃ ይሄው የበግ ለምድ ለባሽ ለምን በየጴንጤው መጋዘን ይሰብካል? ተጋባዥ እንግዳ ሆኖ ይቀርባል? ለምንስ መደበኛው ጴንጤ ተሃድሶ ተብዬውን ሊያጠናክረው የገንዘንና የቁሳቁስ እርዳታ ያደርግለታል? ይሄንን እውነታ ፈጥሬ ሳይሆን በትንሹ እኔ በማውቀው ቅዳሜ ቅዳሜ (8:00AM to 11AM eastern US standard time) በምስራቃዊ አሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር ጠኋት ስምንት ሰዓት ላይ የጀመረ እስከረፋዱ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ (Ethiopian christian plus all) በሚባል የጴንጤዎች የፓል ቶክ ክፍል ውስጥ ፕሮግራም ተይዞላቸው ኦርቶዶክስን ሲሰድቡና ሲያሰድቡ ፤ ድንግልንም ሆነ መላይክትን እንዲሁም ጻድቃንን ሲያንኳጥጡ እንደሚውሉ ማንም ኢትዮጵያዊ የሆነ እዚህ የመናፍቃን የፓል ቶክ ክፍል በመምጣት የፍራሽ አዳሹን እውነተኛ ማንንነት ማወቅ ይችላል ።

ታዲያ ይህ ሁሉ እውነታ ስለናንተ እየታወቀና እያለ ሁለት ቦታ መረጋገጡ ምን ለማምጣት ነው እነ ተሃድሶ? እስቲ ጥያቄያችሁን በጥያቄ ልቅረበው ። ለምን ሁሉ አማረሽ ሆናችሁ? ስለምንስ አንድ ቦታ መርጋት አቃታችሁ? ስለምንስ የኦርቶዶክስን ስም መዋስ አስፈለጋችሁ? እውነተኛ ማንነታችሁን የማያውቅ ያለ ይመስላችሁ ይሆን? ከሆነ በርግጥ በጣም የዋሆች ናችሁ ።

እምነት የመዳን ጉዳይ እንጂ ፣ የቲፎዞ ወይንም የደጋፊ መብዛት ጉዳይ ከመሰላችሁ እጅግ በጣም ተሳስታችኋል ። መንግስተ ሰማይ በቲፎዞ ብዛት ሳይሆን የምትወረሰው በእምነትና በተግባር እንደሆነ የያዛችሁትን ወንጌል መመርመር ያሻል ። ስለሆነ በየጴንጤው መጋዘን ደጋፊ ፍለጋ መንጦዝጦዝና ደጅ መጥናት የመንግስተ ሰማይን ደጃፍ አያስከፍትም ምድራዊ አንቱታን ከሆነ ይቻል ይሆናል ያውም የከንቱ አንቱታ ።

ታዛቢው